የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

**OF THE HARARI PEOPLE REGIONAL STATE**

| | | |
|---|---|---|
| 14 ኛ ዓመት ቁጥር 2<br>14 th Year No. 2 | | ሐረር መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ/ም<br>HARAR March 19 / 2009 |
| ያንዱ ዋጋ ብር 4፡00<br>Unit Price Birr 4፡00 | በሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | የፖ.ሣ.ቁ. 272<br>P.O.Box 272 |


ማውጫ

ደንብ ቁጥር 29/2001

በሐረር ከተማ ህገወጥ የመሬት ይዞታና ግንባታን ለመከላከል የወጣ ደንብ ———————————— ገጽ 477


## ደንብ ቁጥር 29/2001

## በሐረር ከተማ ህገ-ወጥ የመሬት ይዞታና ግንባታን ለመከላከል የወጣ ደንብ

ሕገ-ወጥ ግንባታ ከተማን በእቅድና ስርዓት ለማልማትና ለማሳደግ የሚደረገውን እንቅስቃሴ የሚያዳክም በመሆኑ፣ የከተማ መሬት አጠቃቀምን በመሪ ፕላኑ መሠረት በማስጠበቅ በተገቢው ሁኔታ የቦታ አቅርቦት ሥርዓት በማረጋገጥ ለመኖሪያ ለኢንቨስትመንት አመቺ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ካልታገዘ በስተቀር ህገ-ወጥ ግንባታን ለማስቆም በተናጠል የሚከናወን አለመሆኑን በመገንዘብ፣

ሕገ-ወጥ ግንባታን ለመከላከል ለቀበሌ አስተዳደር የተሰጠ ስልጣንና ተግባርን በተገቢው መንገድ ለማስፈጸም በሚያስችል መልኩ ዝርዝር ደንብ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የሐረሪ ህዝብ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 58/98 አንቀጽ 36 /1 መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹በሐረር ከተማ ሕገ-ወጥ የመሬት ይዞታና ግንባታን ለመከላከል የወጣ ደንብ ቁጥር 29/2001›› ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. “ህገ-ወጥ ግንባታ” ማለት ሕጋዊ ባልሆነ ይዞታ የተካሄደ ግንባታ ወይም ከከተማው ፕላን ውጭ የተሠራ ግንባታ ማለት ሲሆን እነዚህም ያለ ሕጋዊ ፍቃድ የተሠራ አጥር፣ የቤት መሠረት ግንባታ፣ ቤት፣ ህንጻ፣ የፍሳሽ መውረጃ ቱቦ፣ ኮንቴነር፣የገበያ ቦታ ወይም ተንቀሳቃሽ ኪዎስኮችን ያጠቃልላል፡፡
2. “ሕገ-ወጥ ይዞታ” ማለት በከተማው መሬት

ለመስጠት ሥልጣን ካለው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የተያዘ መሬት ነው፡፡

3. "ከተማ" ማለት በሐረር ከተማ አዋጅ ቁጥር 58/1998 አንቀጽ 4/1/ መሠረት የተቋቋመ የሐረር ከተማ ነው፡፡

4. "ከተማ ፕላን" ማለት የሐረር ከተማን የመሬት የመንገድ እና ሌሎች ልዩ ልዩ የአገልግሎት ቦታዎችን አጠቃቀም የሚያሳይ ነው፡፡

5. "የመከላከል እርምጃ" ማለት ህገ-ወጥ ግንባታ መንስኤዎችን ማስወገድ፣ ህገ-ወጥ ግንባታዎችን ከጅምሩ ማስቆምና ማፈረስ፣ ገንቢዎችን ወደ ህግ ማቅረብና ማንኛውንም ህገ-ወጥ የግንባታ እንቅስቃሴ መከላከል ነው፡፡

6. "ቀበሌ አስተዳደር" ማለት በክልሉ መንግስት የወጣ አዋጅ ቁጥር 74/2000 መሠረት የተቋቋመ የቀበሌ አስተዳደር ነው፡፡

7. "ማዘጋጃ ቤት" ማለት የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡

8. "ደንብ አስከባሪ" ማለት ሕገ-ወጥ ግንባታን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ለማከናወን የተመደበ ሠራተኛ ነው፡፡

9. "ክልል" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ነው፡፡

10. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**፡. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በከተማው ውስጥ ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ በተያዙ መሬቶችና በተገነቡ ግንባታዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሕገ-ወጥ ግንባታን ስለመከላከል

**፡. ሕገ-ወጥ ግንባታን ለማስቆም ተቋማት ስለሚኖራቸው ሥልጣንና ተግባር**

1. **ቀበሌ አስተዳደር**

ለቀበሌ አስተዳደር ህገ-ወጥ ግንባታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በክልሉ በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2000 አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 15 መሠረት የተሰጠ ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተለው ዝርዝር ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-

1. በቀበሌው ክልል ውስጥ ያለህጋዊ ፍቃድ መሬት እንዳይያዝ የመከላከል እርምጃ በመወሰድ ያስቆማል፡፡
2. በቀበሌው ክልል በሂደት ላይ የሚገኝ ሕገ-ወጥ ግንባታ እንቅስቃሴን የመከላከል እርምጃ በመውሰድ በጅምሩ ያስቆማል፡፡ ይዞታው እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡
3. በቀበሌው ክልል ሕገ-ወጥ ግንባታ እንዳይፈጸም ይቆጣጠራል፡፡ ይከታተላል የመከላከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
4. በቀበሌው አጠቃላይ የሕገ-ወጥ ግንባታ እንቅስቃሴን ለማስቆም፣የመከላከል እርምጃ የሚወስዱ ደንብ አስከባሪዎችን ይመድባል፡፡ደንብ አስከባሪዎችን ይቆጣጠራል፣ያስተባብራል፣ ይገመግማል፣ አስፋለጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
5. ሕገ-ወጥ ግንባታ አንቅስቃሴ ውስጥ ያገኘውን ማንኛውንም ሰው በቁጥጥር ሥር አውሎ ለሕግ እንዲቀርቡ ያደርጋል፡፡
6. በቀበሌው የሕገ-ወጥ ግንባታ መንስኤዎችን ይለያል ችግሮቹ እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡
7. ሕገ-ወጥ ግንባታን አስመልክቶ ከነዋሪው የሚቀርቡ ጥቆማዎችን ይቀበላል፡፡አጣርቶ ሲያረጋግጥ የመከላከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
8. የቀበሌ ነዋሪውን ህብረተሰብ ስለህገወጥ ግንባታ ይቀሰቅሳል ትምህርት ይሰጣል፡፡
9. በቀበሌው ስለተፈጸመ ሕገወጥ ግንባታና በሕገ-ወጥ ግንባታ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን ዝርዝር በመመዝገብ መረጃ ይይዛል፡፡
10. በቀበሌው ሕገ-ወጥ ግንባታን ለማስቆም በተወሰደ የፈረሳ እርምጃ የተገኙ የግንባታ እቃዎችና መሥሪያ መሣሪያዎችን ይወርሳል፡፡ ለማዘጋጃ ቤቱ ያስረክባል፡፡
11. ህገ-ወጥ ግንባታ መሆኑ አጠራጥሪ ሆኖ ሲገኝ ማዘጋጃ ቤቱ በቀበሌው አስተዳደር ሲጠየቅ ህገ- ወጥ መሆን አለመሆኑን አረጋግጦ ሲያሳውቀው ወዲያውኑ እርምጃ ይወስዳል፡፡
12. ሕገ-ወጥ ግንባታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል ከማዘጋጃ ቤቱ ጋር ተባብሮ ይሰራል፡፡ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይሰጣል፡ ይቀበላል፡፡

13. ህገ-ወጥ ግንባታ በመፍረሱ ምክንያት ቀበሌው ያወጣቸውን **ወጪዎች** ህገ-ወጥ ገንቢው ላይ በፍትሀብሄር **ህግ መሰረት** ያስመልሳል።

2. ማዘጋጃ ቤት

ማዘጋጃ ቤቱ ህገ-ወጥ ግንባታን ለመከላከል የሚከተለው ዝርዝር ስልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል።

1. በከተማው ህገ-ወጥ ግንባታ የሚወገድበትን ሁኔታን አስመልክቶ፣ **ጥናት ያካሄዳል**፤ መፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል።
2. ሕገ-ወጥ ግንባታን ለመከላከል እንዲቻል ከቀበሌ አስተዳደር አካላት ጋር በጋራ ተባብሮ ይሠራል፤ ድጋፍና እገዛ **ያደርጋል**።
3. በከተማው ሕገ-ወጥ ግንባታን ይለያል፣ በዝርዝር እንዲመዘገቡ ያደርጋል።
4. በከተማው ስለ ሕገ-ወጥ ግንባታን አስመልክቶ በብዙሃን መገናኛ ቅስቀሳ ያደርጋል። የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ህብረተሰቡን ግንዛቤ ያስጨብጣል ትምህርት ይሰጣል።
5. ሕገ-ወጥ ግንባታ የመከላለከል እርምጃ በቀበሌዎች መከናወኑን በቅርበት ይከታተላል ይቆጣጠራል። አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ልውውጥ ያደርጋል።
6. በከተማ ሕገ-ወጥ ግንበታን ለመከላከል እንዲቻል በቀበሌዎች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር ድጋፍና እገዛ ያደርጋል።

7. ህገ-ወጥ ግንባታ መሆኑ እንዲረጋገጥ በቀበሌው ሲጠየቅ አረጋግጦ ወዲየውኑ ያሳውቃል።

3. መደበኛ ፖሊስ

ሕገ-ወጥ ግንባታን በመከላከሉ ረገድ መደበኛ ፖሊስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. በከተማው ሕገወጥ ግንበታን ለማስቆም እንዲቻል በህገ-ወጥ ተግባር የተሳተፉ ገንቢዎችን በቁጥጥር ሥር አውሎ ወደ ሕግ እንዲቀርቡ ያደርጋል።
2. ደንብ አስከባሪዎች ሕገ-ወጥን ለመከላከል እንዲቻል ለሚያቀርቧቸው የትብብር ጥያቄዎች የመደበኛ ፖሊስም ሆነ የፖሊስ ጣቢያ የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

5. የእርሻ መሬትን ለህገ-ወጥ ገንቢዎች ማስተላለፍ የተከለከለ ስለመሆኑ፣

1. በከተማ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ገበሬዎች ለእርሻ ተጓዳኝ አገልግሎት የሚጠቀሙበትን ይዞታ ለይቶ የሚያመለክት ጊዜያዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ማዘጋጃ ቤቱ ይሰጣል፣
2. ለእርሻና ተጓዳኝ አገልግሎት የተሰጠን መሬት በማንኛውም መንገድ ሕገ-ወጥ ግንባታ ለሚገነባ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፣
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገወጥ ግንባታ ተካሂዶበት በተገኘ መሬት ላይ ግንባታው ከፈረሰ በኃላ ገበሬው የይዞታም ሆነ የካሣ ይገባኛል ጥያቄ ማንሣት አይችልም። ማዘጋጃ ቤቱ መሬቱን በቀጥታ ወስዶ ለሚፈልገው አገልግሎት ያውላል።

6. ለሕገ-ወጥ ግንባታ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎች ጥበቃ ስለማድረግ

ማዘጋጃ ቤቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለልማት የማይፈልጋቸውን መሬቶች ለይቶ በፕላን ላይ በማስፈር ተገቢው ክትትልና ጥበቃ እንዲደረግ አግባብ ላላቸውየቀበሌ መስተዳደሮች ማሳወቅ አለበት። የቀበሌ አስተዳደር አካላትም ተለይቶ የተገለፀላቸውን መሬት ጠብቀው የማቆየት ኃላፊነት አለባቸው።

7. ስለ ሕገ-ወጥ ግንባታ ንብረቶችና የመስሪያ መሣሪያዎች

1. ሕገ-ወጥ ገንቢው በራሱ ጉልበትና ወጪ ግንባታውን ካላፈረሰ በስተቀር በመከላከል እርምጃ እንዲፈረስ የተደረገ ንብረት ለመንግስት ገቢ ይሆናል።
2. በሂደት ላይ ያለን ህገ-ወጥ ግንባታ ለማስቆም በተወሰደ የመከላከል እርምጃ የተገኘ የመገንቢያ መሥሪያ መሣሪያዎች ለመንግስት ገቢ ይደረጋል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ገቢ የተደረገ ንብረት ይመዘገባል።
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ገቢ የተደረገ ንብረት በጨረታ ይሸጣል። በሽያጩ የሚገኘው ገቢ ለደንብ አስከባሪዎች ማበረታቻና ለመከላከል ሥራ ወጪ ይውላል።

8 **ቅጣት**

1. ህገ-ወጥ ግንባታ ፈፃሚዎችን በተመለከተ፡-

ሀ. በህገ-ወጥ ገንቢው ላይ የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ የእርሻ መሬቱ ላይ ህገ-ወጥ ግንባታ ያካሄደ ወይንም ለህገ-ወጥ ገንቢ አሳልፎ የሰጠ ገበሬ ፤

ለ. ህገ-ወጥ ግንባታ ሲያስፋፋ የተገኘ ሰው፣

ሐ.ህገ-ወጥ ግንባታ ለማስቆም የሚደረገውን እንቅስቃሴ ያደናቀፈ፣ለግንባታው ድጋፍ የሰጠ ትብብር ተጠይቆ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ለፈጸመው የደንብ መተላለፍ ተግባር እስከ ብር 300 የገንዘብ መቀጮ ወይንም እስከ አንድ ወር በሚደርስ እስራት ይቀጣል፤

መ.የመንግስት መሬት ወሮ የያዘ ወይም ህገ-ወጥ ግንባታ የፈፀመ በወንጀል ህግ ይቀጣል፡፡፤

2. አስፈፃሚ አካላትን በተመለከተ፡-

ሀ. ህገ-ወጥ የቦታ መያዝና ግንባታ መፈፀሙን እያወቀ እርምጃ ሳይወስድ የቀረ ጉዳዩ የሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር አካል፣

ለ. ትብብር ተጠይቆ ያለበቂ ምክንያት ትብብር ያላደረገ የፓሊስ አካል ለፈጸመው የደንብ መተላለፍ ተግባር እስከ ብር 300.00 የገንዘብ መቀጮ ወይንም እስከ አንድ ወር በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ወይም መንግስታዊ አካል ይህን ደንብ በማስከበር ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. **ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች**

1. በክልሉ መንግስት ስለ ህገ-ወጥ ግንባታን የሚቆጣጠር እና የሚከላከል ግብረ ሀይል ለማቋቋም የወጣ ደንብ ቁጥር 7/1994 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

11. **መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ሐረር መጋቢት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

ሙራድ አብዱልሃዲ

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት